# መልእክት

ዉድ የተከበራችሁ ወገኖቼ፣
ጤና ይስጥልኝ
በወያኔ እስር ቤት የሚማቀቁትን ንፅህ መሪዎቻችንና ወገኖቻችንን፣ በጠቅላላው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን ስቃይ በማሰብ ልባችን በጥልቅ ሃዘን ተውጦ እያለ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡ ይህ ሁኔታ ተለውጦ ነፃነት እስከሚመጣ ድረስ እኛም አሁን ካለንበት የህሊና ስቅይ ልንድን አንችልም፡፡

ባለፈው ግንቦት ወር ምርጫ ፣ ሕዝባችን የወያኔን መንግሥት በማያወላውል መልኩ አንቅሮ የጣለው መሆኑን ቢታወቅም የመረጠውን የራሱ የሆነውን መንግሥት ገና አልተረከበም፣ ለመረከብ የሚያመራ የመጀመሪያው እርምጃ መሪዎቹና የቀሩት የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ማስድረግ ነው፡፡ ይህንንም ከዳር ለማድረስ የተጀመረው ስላማዊ የተቃውሞ ትግል አሁንም እንደበፊቱ ወኔ በተምላበት መልኩ መቀጠል አለበት፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ የኛ ድርሻ የደመቀ የተቃውሞ የሰላማዊ ሠልፍ ማካሄድ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ባለፈው ጥር ወር ላይ ተካሂዶ የነበረው የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ተውካዩች ጉብዔ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ሁለተኛው ጉዔ በሚፈፀምበት ማግሥት ማለትም ግንቦት 8 (May 16) ቀን በዋሽንግተን ከተማ ሠፊና የደመቀ የተቃውሞ ሠላማዊ ሠልፍ እንዲደረግ ጥሪ ተላልፎአል፡፡ በዚሁ አንፃር ደግሞ ሌሎች ድርጅቶች በዚሁ በዋሽንግተን ከተማ ለግንቦት 7 (May 15) ቀን ከእኛ ጥሪ በኋላ ተመሳሳይ ጥሪ ማድረጋቸውን ተረድተናል፡፡

ሁለቱም ቀኖች፣ ግንቦት 7 እና 8 ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ቀኖች ናቸው፡፡ ግንቦት 7 ቀን፣ 26 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያኖች ወጥተው የምርጫ ድምፃቸውን የሰጡበትና የሚፈልጉትን የቅንጅትን አመራር መርጠው አርነትን የተቀናጁበት የድል ቀን ስለሆነ እንደታላቅ የሕዝብ በዓል ሆኖ በርችት በመድፍ ተኩስና በልዩ ልዩ ስነስርአት ደምቆ መከበር እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ድል ዓይናችንን ጨፍነን ስንከፍት፣ ገና በማግስቱ በግንቦት 8 ደግሞ አምባገነኑ ወያኔ የሕዝቡን መብት በመሣርያ ኃይል ጠቅሎ በመንጠቅ "አሸናፊ እኔ ነኝ" ብሎ ያወጀበት ቀን ነው፡፡ ከዚህ በላይ የሚነሳው ጥያቄ በግንቦት 7 እና 8 በተለያዩ ከተማዎች የተጠሩት ሠልፎች ዓላማ ልዩነት ምንድን ነው የሚለው ነው፡፡

- የድሉን በዓል ለማክበር/ለማሰብ ከሆነ ትክክለኛው ቀን ግንቦት 7 ይሆናል፡፡
- ድላችንን የተነጠቀበትን ቀን ለመቃወም፣ የሕዝቡን ድምፅ ለማስከበር፣ የታሠሩትን መሪውቻችንና ወገኖቻችንን ያለምንም ቅድመ ሁኔት ይፈቱልን፣ ፍትህና ርትዕ በኢትዮጵያችን ይውረድ ብለን የሮሮ ድምፅ የምናሰማበትና የውጭ መንግሥታትን ድጋፍ የምንጠይቅበት ሠልፍ ከሆነ ቀኑ ግንቦት 8 ነው፡፡

በአጭሩ ቅንጅት በሁለቱም ቀኖች ላይ ከላይ በተገለፀው መልክ ያምናል፡፡ አሁን ዋሽንግቶን ላይ ባለው ሁኔታ ሠልፉ በ7 ብቻ በዓል በማክበር ሳይወሰን፣ ትግሉን ቀጥሎ፣ በ8 ደግሞ የተቃውሞ ሠልፍ እንዲደረግ ቅንጅት ይደግፋል፡፡ የሁለቱን ቀናት አሰላለፍ በተለያየ መልክ ይካሄዳል፡፡

ስለዚህ የተከበራችሁ ዉድ ወገኖቼ ይህ ጥር የያንዳንዳችሁና የሁላችንም ስለሆነ እንደተለመደው በጋለ መንፈስ እንድናደምቀው አደራ አደራ እላለሁ፡፡ እግዚአብሔር ይርዳን

አመሰግናለሁ፡፡
ሻለቃ ዮሰፍ ያዘው